# ከዓለም አቀፍ የኢሮብ ዲያስፖራ ኮሚቴ (ዓአኢዲኮ)

## የትብብር ጥሪ ለኢትዮጵያዊያን፣

irobcomm@gmail.com

በግንቦት 1990 ዓ ም የኤርትራ መንግስ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ግዛቶች በመውረር ጦርነት እንደከፈተብንና በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን ቀፎው እንደተነካበት ንብ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከጫፍ እስከጫፍ በመነሳሳት፣ የመላው ኢትዮጵያ ልጆች ደም ባንድነት ተቀላቅሎ በመኊረፍ ከፍያለ መስዋእትነት ከፍለው የኤርትራ ወራሪ ኃይል ድባቅ በመምታት ያንበረከኩበትና የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት በጦር ግንባረ በማሸነፍ ያረጋገጡበት ሁኔታ እንደነበር ይታወሳል።

ሆኖም፣ በጦር ሜዳ የተረጋገጠው ድል እዛው ሜዳ ላይ በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መረጋገጥና መጠናቀቅ ሲገባው፣ የወቅቱ የኢትዮጵያ ጠ/ሚ ነበር አቶ መለስ ዜናዊ ጦርነቱ እንዲቆም ትእዛዝ በማስተላለፍ አክሽፈውታል። አቶ መለስ ያን የሡራዊታችንን ግስጋሴ ያስቆሙት እጅግ ወሳኝ ምእራፍ ላይ በነበረበትና የኤርትራ የወደፊት እጣ ፈንታ በኢትዮጵያ ዙርያምላሽ ጥቅሞች በዘላቂነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ምዕራፍ ላይ በነበረበት ደረጃ ላይ እያለ ነበር። ጦርነቱ እንዲቆም ትእዛዝ የተላለፈው የኤርትራ ጦር ለሁለት ዓመታት መሬት በመቆፈርና በታላላቅ የዓለም መገናኛ ብዙኃን ሳይቀር የማይደፈር የተባለላቸው ከባድ ምሽጎችን ለማፈራረስ ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈል በወሳኝ መልኩ የኤርትራ ጦር እግሬ አውጪኝ ሽሽት በያዘበት፣ ሲቪል ኢትዮጵያውያን ከየቤታቸው በኤርትራ ፀጥታ ኃይሎች ታፍነው ተወስደው መዳረሻቸው ያልታወቀበት፣ በዓሰብና ምፅዋ ወደቦች የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥትና ግለሰብ ኢትዮጵያውያንኖች ንብረቶች የተወረሱበት፣ ኮሎኔል በዛብህ ጴጥሮስ ሲያበሩት የነበረው አይሮፕላን ተመቶ በጃንጥላ ወርደው የኤርትራ መንግሥት የጦር ምርኮኛ የነበሩበት፣ የዓይደር ህፃናት በክላስተር ቦምብ መደብደብ፣ የዓዲግራት የእርዳታ ኮሚሽን እህል ማከማቻ ተፈናቃዮች እርዳታ ለመውሰድ በተሰለፉበት ሰዓት ላይ በአየር የተደበደቡበት፣ . . . . ወዘተ. ሁኔታ ላይ ነበር ጦርነቱ ማኽል ላይ እንዲቆም የተደረገው። የህወሓት መሪዎች ቢጠቀሙበት ኖሮ ኤርትራን በሚመለከት የፈጸሟቸው ስህተቶችን ለማረም ሻዓቢያ የተመቻቸ እድል ፈጥሮላቸው ነበር። ሆኖም፣ አልተጠቀሙበትም ወይም ሊጠቀሙበት አልፈለጉም። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ዘርፈ ብዙ ችግሮች ተገቢ መልስ በማግኘት ጦርነቱ የኢትዮጵያ ዘላቂ ድል በማብሰር እዛው ጦር ሜዳው ላይ ሊቋጭ ሲችል፣ ምንም ግንዛቤ ሳይሰጠው የታለፈበት ምክንያት ምን ሊሆን እንደሚችል ሚስጢሩ የሚፈታው ምናልባት የታሪክ ተመራማሪዎች ይፋ ሲያወጡት ይሆናል። ድሮ ህወሓት ከደርግ ጋር ይዋጋ በነበረበት ጊዜ "እየተዋጋን እንደራደራለን፣ እየተደራደርን እንዋጋለን" የሚል መፈክር አንግቦ ይጓዝ ነበር። ያ መፈክር የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጊዜ የት እንደተቀበረም አይታወቅም። የሆነ ሆኖ ጦርነቱ በወረራ የተያዙብን ሉዓላዊ የኢትዮጵያ ግዛቶች ባለቤትነት ባላረጋገጠ መልኩ መገባደዱና ሠራዊታችን ግስጋሴውን እንዲገታ መታዘዙ ያልተፈታ እንቆቅልሽ ነው።

ይባስ ብሎ ያ ሁሉ የኢትዮጵያዊያን ውድ ሕይወት የተከፈለበትና በአውደ ውጊያ በአሸናፊነት መንፈስና የሞራል ልእልናን ወደፊት በመገስገሰ ላይ የነበረውን ሠራዊት ግስጋሴውን እንዲገታ ነበር የታዘዘው። ጦርነቱ በኣቶ መለስ ትእዛዝ እንዲቆም ከተደረገ በኋላ፣ በኢህአዴግ መሪዎች ውይይት ተደርጎበት ለድምጽ ቀርቦ የአቶ መለስ ደጋፊዎች በድምጽ ብልጫ በማሸነፋቸው አልጀርስ ስምምነት ጠ/ሚ መለስና አቶ ኢሳያስ አፈወርቂ በተጨባበጡበት እንዲፈረም ሆነ። አሁን የአልጀርስ ስምምነት ተብሎ የሚታወቅ የኢትዮጵያን ሽንፈት "ያበሰረውም" ይህ ያኔ የተፈረመው ሰነድ ነው። በዚህ ሰነድ አማካኝነትም ከሁለት ዓመታት የኤርትራ ወረራ በኢትዮጵያዊያን ጀግኖች

ደም በጦር ግንባር ፍልሚያ የተከበረው ጻር ድንበራችን አልጀርስ ላይ እንዲከሸፍ ተደረገ። ለምን ያንን ሰነድ መፈረም አስፈለገ የሚለው ጥያቄም ገና መልስ አላገኘም። ይህን ተከትሎ የህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ ለሁለት መሰንጠቅ፣ የአቶ መለስን በህወሓትና ኢህአዴግ ውስጥ ብቸኛ አምባገነን መሪ ሆነው እንዲወጡና የፈቀዱትን እንዲያደርጉ አስቻለ።

ከዛም የአልጀርሱን ሰነድ መሠረት ያደረገ ገላጋይ ፍርድ ቤት Eritrea Ethiopia Boundary Commission ተብሎ የሚታወቅ የድንበር ኮሚሽን ተቋቁሞ እስከዛሬ ድረስ እልባት ያልተገኘለት ፍርደ ገምድል ውሳኔ በማስተላለፍ ተቋጨ።

በዚህ የሄግ ኮምሽን ፊት ኢትዮጵያን የወከሉ ኢትዮጵያዊያን ሶስት ሲሆኑ፣ እነሱም፣ 1ኛ. አቶ ሥዩም መስፍን የወቅቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር 2ኛ. አምባሳደር ፍስሃ ይመር 3ኛ. አቶ ሰይፈሥላሴ ለማ በውጭ ጉዳይ የሕግ አማካሪ ሲሆኑ ሌሎች በሙሉ የውጭ ዜጎች ነበሩ። ኢትዮጵያን ወክለው እዛ የተገኙት ሶስቱ ኢትዮጵያውያን ለኮሚሽኑ መቅረብ የነበረባቸው ማስረጃዎች ለማቅረብ አለመቻላቸው ወይም አለመፈለጋቸው ላይ የታየው ክፍተት ከምን እንደሚመነጭ መጣራት አለበት የሚል ፅኑ እምነት አለን።

<u>ለምሳሌ</u>፣ የኢሮብ መሬት ድንበርን በሚመለከት በአፄ ሚኒልክና ጣሊያን መካከል ተደርጓል የተባሉት ሶስት ውሎች ውስጥ በአንዱም አልተካተተም፣ ተግባር ላይም አልዋለም። የኢሮብ ህዝብም ሆነ የኢሮብ መሬትም ላንድም ቀን የኢጣልያ ግዛት ውስጥ የተካተተበት ታሪክ የለም። ጣሊያኖች በወቅቱ የነበሩ የኢሮብ ባለሥልጣናትን ለማግባባትና የኢሮብ ወረዳን ግዛታቸው ወደ ነበረችው ኤርትራ ለማጠቃለል ያደረጉት ሙከራ የከሸፈውም፣ የተጠየቁት የኢሮብ ባላባቶች የኢሮብ ህዝብ ከኢትዮጵያዊነት ውጭ የሚያውቀው ሌላ ዜግነትም ሆነ ገዢ እንደሌለና እንደማይኖርም በግልጽ በመንገርና በማስጠንቀቅም ጭምር ስለመለሷቸው ነበር። ራስ ስብሓት ራሳቸው (ኢሮብ ናቸው) የኢሮብ ህዝብ ከትግራይ ውጭ ሆኖ እንደማያውቅና አሁንም ኢትዮጵያዊ ሆኖ እንደሚቀር ያወጁበትና ያስጠነቀቁበት ሁኔታ እንደነበረም በታሪክ የተመዘገበ ሃቅ ነው። እንዲሁም እነ ብላታ ናይዝጊ ወልደገሪማና ቀኝአዝማች ሺፋረ ወልደገሪማ ያሉ የኢሮብ መሪዎች ያኔ የጣልያን እና የኢትዮጵያ ይባል የነበረው የድንበር ኮሚሺን ጋር በመወያየት ያስቀሩት ሉዓላዊ የኢትዮጵያ ግዛት እንደሆነም ግልፅ ነው። በሄግ ኮሚሽን ፊት ግን የተወሰነ የኢሮብ መሬትን አስመልክቶ ኤርትራ “ግዛቷ መሆኑን የሚያስረዳ” ማስረጃ ስታቀርብ በኢትዮጵያ በኩል ግን ምንም ማስረጃ እንዳልቀረበ የኮሚሽኑ ውሳኔ ያትታል። ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለ እነ አቶ ሥዩም መስፍን ሊመልሱት ይገባል። በኢሮብ መሬት ላይ በምንም ዓይነት ተአምር ኤርትራ ሕጋዊ የሆነ የባለቤትነት ማስረጃ ማቅረብ የምትችልበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም። የሆነ ፎርጅድ(የሐሰት) ማስረጃ አቅርባም ከሆነ እነ አቶ ሥዩም መስፍን ማስረጃው እንዲመረመር ኮሚሽኑን መጠየቅ ይችሉ ነበር። አልጠየቁም፣ ለምን? መልስ የሚሻ ጥያቄ ነው። (ለነገሩ በሚል ብናነሳውም በአፄ ሚኒልክና ጣልያን መካከል ተደርጓል የተባሉት የ1900, 1902, 1908 ዓ ም ፈ ውሎች ራሳቸው በ1928 ዓ ም ጣልያን ኢትዮጵያን ሲወር የተጣሱ መሆናቸው ልብ ሊባል ይገባል)!

ይህ ሁሉ ታልፎ ኢትዮጵያውያን ከውጭም ከውስጥም የአልጀርሱን ሰነድም ሆነ በዛ ሰነድ መሠረት የተቋቋመው ኮሚሽንን አጥብቀው ቢቃወሙትም ሰሚ በማጣታቸው ሁላችን የምናውቀው የተውሸለሸለው የሄግ ኮሚሽን ውሳኔ ይፋ ሆነ። አቶ ሥዩም መስፍንም ያለ አንዳች ሓፍረት “በጦር ግንባር ያስመዘገብነው ድል በሕግ ፊትም ደገምነው። የጠየቅነው ብቻ ሳይሆን ያልጠየቅነውም መሬት ተበይኖልናል” በማለት የኢትዮጵያ ህዝብን አስጨፈሩ። ነግቶ ፀሓይ ብርሃኑዋን እንደፈነጠቀች ግን እውነታው ለኢትዮጵያ ህዝብ መታየት ጀመረ። ህዝብም በየአከባቢው ማጉረምረምና መቃወም ጀመረ። የህወሓት መሪዎች ግን ዓይናቸውን በጨው አጥበው ያ የአቶ ሥዩም መስፍን የአሸንፈናል ቀረርቶ ግልጥልጥ ብሎ ለህዝብ በይፋ በታየበት ወቅት ሳያፍሩ

በኢሮብ ወረዳ ውስጥ ካድሬዎቻቸውን በማሰማራት ስለተፈረደብን መሬት ለኤርትራ ልናስረክብ ነው የሚል መልእክት ህዝብ እየሰበሰቡ መስበክ ጀመሩ። ከኢሮብ ህዝብ ያገኙት መልስ ግን አስደንጋጭ ሆነባቸው። ይኸውም፣ እንኳን መሬታችን ድንጋይ ተንሸራቶ ወደ ኤርትራ መሬት ቢወድቅ አንተወውም የሚል ነበር። በዚህ ምክንያትም፣ የአቶ መለስ ዜናዊ የአምስት ነጥቦች የመደራደርያ ሓሳቦች ቀረቡና ፕረዝደንት ኢሳያስ አሻፈረኝ በማለታቸው ችግሩ እስከዛሬ ድረስ ሲጓተት ቆይቶ ዛሬ የችግሩ ተረካቢ ጠቅላይ ምንስትር ዶ/ር ዓቢይ አሕመድ ሆኗል።

ኢህአዴግ ዶ/ር ዓቢይ አሕመድን መርጦ የኢትዮጵያ ጠ/ሚ ሆነው እንደተሰየሙ፣ የኢህአዴግ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የአልጀርስን ስምምነት ያለምንም ቅድመ ሁኒታ ተግባራዊ ለማድረግ ኢትዮጵያ ዝግጁ እንደሆነች አስታወቀ። ይህ መግለጫ እንደወጣም የኢሮብ ህዝብ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ከዳር እስከዳር ተንቀሳቀሰ። በዳውሃን፣ በምዕራብ ኢሮብ፣ በዓዲግራትና መቐለ ደማቅ ሰላማዊ ሰልፍ (ሰላማዊ የሚለው ቃል አንዳ አንድ ተውሳኮች እንደሚሉት ዓይነት ሳይሆን የእውነት ሰላማዊ እንደነበረ ሊሰመርበት ይገባል) በማድረግ ተቃውሞውን ያሰማ ሲሆን አዲስ አበባ ውስጥ ሊደረግ ታስቦ የነበረውን ግን አንዳ አንድ አሉባልተኞች በለመዱት ውሸት ቀድመውን ሰልፉ የህወሓት መሪዎች የዶክተር ዓብይን የለውጥ እንቅስቃሴ በመቃወም የሚያዘጋጁት እንደሆነ በማስመሰል ያልሆነ ፕሮፓጋንዳ በመንዛትና ያልሆነውን እንደሆን አድርገው ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን መነሻችን እንዲጠራጠሩ ለማድረግ በመቻላቸው፣ በመቃወምም ሆነ በመደገፍ በሰላማዊ መንገድ ድምጻችንን የማሰማት ሕገ-መንግሥታዊ መብት እንዳለን ብናውቅም የአሉባልተኞችን ምኞት ላለማሳካት ለጊዜው እንዲተላለፍ መደረጉ ይታወሳል። በውጭ አገሮች የሚኖሩ ኢሮቦዎችም "ዓለም አቀፍ የኢሮብ ዳያስፖራ ኮሚቴ" በማቋቋም በዚህ ኮሚቴ አስተባባሪነት ተቃውሞዋቸውን በወብሳይቶችና በሌሎች ማኅበራዊ መገናኛናዎች አስተጋብቷል፣ እያስተጋቡም ይገኛሉ።

አንዳ አንድ እስከ ዛሬ የት ነበራችሁ የሚል ጥያቄ በየዋህነት ለምታነሱ ወገኖቻችን፣ የኢትዮ-ኤርትራ ዳር ድንበር ጉዳይ መነሳት ከጀመረበት ዕለት ጀምሮ ተግባሮቻችንን መከታተልና ያለመከታተል ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር አንድም ቀን ተዝናንተን የተቀመጥንበት የለም። ዛሬ ላይ ደርሰው ኡኡታችንን ለማስተጋባት መድረክ የነሱን ወብሳይቶች ጭምር መግለጫዎቻችንን ያወጡት ነበርና አሉባልተኞቹ ትግላችንን ይከታተሉ እንደነበር ለመገንዘብ የሚቻል ቢሆንም፣ ብዙኃኑ ልብ ሳይለው ቀርቶ ካልሆነ ያልጮህንበት ጊዜ አልነበረም። ከመቶ በላይ የሚሆኑ በሻዓቢያ ተወስደው ይኸው 20 ዓመት ስላስቆጠሩ ዜጎቻችንና ስለ ዳር ድንበራችን ያቀረብናቸው አብየቱታዎቻችን ዛሬም www.irobmablo.orgና www.irro.org ወብሳይቶች በመግበት ስናደርጋቸው የነበሩ እንቅስቃሴዎቻችንን በከፊል ማየት ይቻላል። ሆኖም፣ ስለዜጎቻችንም ሆነ ስለ ዳር ድንበራችን ተጨንቆ ተገቢ ምላሽ የኢትዮጵያ መንግሥትም ሆነ ሌሎች የሚመለከታቸው ዓለም-አቀፍ መንግሥታት፣ እንዲሁም ለሰብአዊ መብት እንሟገትአለን የሚሉ ድርጅቶች ለአቤቱታችን መልስ አልሰጡንም እንጂ፣ አቤት ማለታችንን አላቆመም፣ አያቆምም።

አሁን ዶ/ር ዓቢይ ጠ/ሚ ከሆኑ በኋላ እንደተነሳሳን፣ የለውጡን እንቅስቃሴ ለመቃወም እንደተነሳን ተደርጎ የሚነዛው አሉባልታ ፈጽሞ የኢሮብ ህዝብን የሚመለከት አይደለም። ሉዓላዊ መሬታችንና ህዝባችን ለተወሰኑ ወገኖች አምሮት እደሚለወጥና ኢትዮጵያዊነታችን ለገበያ እንደሚቀርብ እንደዛሬው ግልብጭ ብሎ ቢነገረን ስናደርገው የቆየነውና ዛሬም የምናደርገው ማድረጋችን አይቀሬ ነበር። ይህ ከኢሮብ ህዝብ የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ ጋር የተያያዘ እንጂ አንዳ አንዶች እንደሚያወሩት ከዶ/ር ዓቢይ ሹመት ጋር ፈጽሞ የሚገናኝ ነገር የለውም። የኛ ጥያቄ የሥልጣን ጥያቄ ሳይሆን እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ አናሳ ብሔረ-ሰብ የመኖርና ያለመኖር ጥያቄ ነው። የዶ/ር ዓቢይ ጠ/ሚ መሆን የኢሮብ ብሔረ-ሰብን ኢትዮጵያዊነት የሚገፍ መሆን የለበትም አይሆንምም።

ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ የኢሮብ አናሳ ብሔረ-ሰብ ህልውናን የሚፈታተን እርምጃ እንደሚወሰድ በይፋ ሲነገረን ለመንግሥታችን ችግራችንን እንዲረዳልን አቤቱታ ማቅረባችን እንደ ነውር ለምን ሊቆጠርብን እንደቻለ ለማመን ቸግሮናል። የኢሮብ ህዝብ ስለኢትዮጵያዊነት ሲነሳ የሚደመር እንጂ አንዳንድ ኢትዮጵያዊያን ሊሂቃን በማኅበራዊ መገናኛናዎችና በተለያዩ ሬድዮ ጣቢያዎች አቶ ኢሳያሳን እነዚህ የድንበር ነዋሪ ህዝቦችና መሬቶች እባክህ ፈጥነህ ውሰድልን እያሉ የሚማፀኑት ዓይነት ህዝብ አይደለም። የኢሮብ ህዝብ ኢትዮጵያዊነትን ለማቆየት ከነዚህ ሊሂቃን ነን ባይ ወላዋይ ራስ ወዳዶች በላይ መስዋእትነት የከፈለ ህዝብ እንደሆነ መታወቅ አለበት። የኢሮብ ህዝብ የዶ/ር ዓቢይ አዎንታዊ እርምጃዎችን ከልብ ቢደግፍም መሬታችንና ህዝባችን ለኤርትራ ተላልፎ መሰጠትን ግን ከመሸጥ ለይቶ አያየውም። ማንም መጣ ማንም፣ የኢሮብ ህዝብን ኢትዮጵያዊነት አሳልፎ ለመስጠት የሚሞክር ቢመጣ መከፈል ያለበትን ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ መሆኑ ጠላትም ሆነ ወዳጅ ልብ ብሎ ሊገነዘበው ይገባል።

በዚህ መሠረትም የኢሮብ ህዝብ ባሁኑ ሰዓት በአንድ ድምፅ ለአንድ ዓላማ ቆሟል። በዚህ መሠረትም በውጪ የሚኖሩ የኢሮብ ተወላጆች ዓለም አቀፍ የኢሮብ ዳያስፖራ ሕብረት በማቋቋም አገር ቤት እየተካሄደ ያለውን የኢሮብ ህዝብ ትግል በቻለው ሁሉ ለመደገፍ በመስራት ላይ ይገኛል።

የኢሮብ ህዝብም ሆነ ዓለም አቀፍ የኢሮብ ዳያስፖራ ሕብረት ዓላማ አንድና አንድ ነው።
ይኸውም፣ ራስን ከጥፋት መከላከል ነው።ባህሉን፣ቋንቋውንና ኢትዮጵያዊነቱን አስፈላጊ ሲሆን እንደ ወትሮው መስዋእትነት ከፍሎም ቢሆን ማስጠበቅ ነው።በዚህ ነጥብ ላይ ድርድር ሽምግልና የሚባል ነገር ፍጹም አይኖርም። በመሆኑም፣ ጥሪያችን ማነኛውም ኢትዮጵያዊነትን የሚያከብር ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲያዊ ኃይል አቅሙ በሚችለው ሁሉ ከጎናችን እንዲቆም ነው። በዚህ በኩል ያወጣናቸው መግለጫዎችን በድረ-ገጾቻቸው ላይ በመጫን የተባበሩን ድረ-ገጾችን እንዲሁም ድምጻችንና ብሶታችንን ለማሰማት እድሉን ለሰጡን የተለቭዥንና የሬድዮ ጣቢያዎችን ሳናመሰግን ማለፍ አይቻለንም።ፕሮፌሰር ተኮላ ሐጎስ በዓይጋ ድረ-ገጽ፣ (http://www.aigaforum.com/article2018/contra-border-demarcation.htm) ዶ/ር ኃሌ ላረቦ በኢትዮ-ሚዲያና http://www.ethiomedia.com/1000dir/ethiopianism-and-ethiopia.pdf ዶ/ር ገላውዴዎስ አርኣያ በሲኒት ራዲዮ http://tigray.net/2018/06/08/%e1%88%ac%e1%8b%b5%e1%8b%ae-%e1%88%b5%e1%8a%92%e1%89%b5-%e1%8a%a5%e1%8b%8b%e1%8a%93%e1%8b%8a-%e1%8a%a9%e1%8a%90%e1%89%b3%e1%89%b5-%e1%88%83%e1%8c%88%e1%88%ad%e1%8a%93-june-08-2018-interview-wit/ እንደ ቅደም ተከተላችሁ ለጻፋችሁት ምስክርነትና በቃለ መጠይቅ ለሰጣችሁን ድጋፍ ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን። ለወደፊቱ ትብብራችሁን እንዲትቀጥሉም አደራ እንላለን።

ኢትዮጵያዊነት የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ እያደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች ላይ ከመታየትና ለብሶ ከማንጎራደድ በላይ እንደሆነ ግንዛቤ ማግኘት ይኖርበታል። አንዳንድ ተለቪዥን ጣቢያዎችና የነጻነት ታጋይ አክቲቭስት ነን ባይ ግለ-ሰቦች በሚያሰራጩት የውሸት ፕሮፓጋንዳ የተደናገራችሁ የድረ-ገጽም ሆነ የራዲዮ ባለቤቶች ጥሬውን ከገለባው ለመለየት የምትችሉት እውነቱን ከባለቤቱ ማግኘት ስትችሉ ብቻ መሆኑን እንዳትዘነጉ ለማሳሰብ እንወዳለን። የኢሮብ ህዝብ ኢትዮጵያዊነት ላይ ተደራድሮ አያውቅም ዛሬም ነገም አይደራደርም።

ለዶ/ር ዓቢይ መንግሥት የምናሳስበውና የምንማጸነው፣

1. ነገሮች መቸና እንዴት እንደተበላሹ ከላይ በዝርዝር ሰፍሯል። ሆኖም፣ አንዴ የተፈጸመ ስሕተት ስሕተት መሆኑ እየታወቀ በዛው በስሕተቱ መንገድ መጓዝ ድጋሚ ስሕተት ከማስከተል ውጪ የሚፈይደው ነገር የለም። ስለሆነም፣ ጥሪያችንና ተማጽኖአችን ስህተቱ በጊዜ እንዲታረም ነው። መሬታችንና ህዝባችንን ለኤርትራ በማስረከብ የኢሮብ ህዝብ ህልውና የሚያጠፋ ውል መተግበር የለበትም። የአልጀርስ ውል ተግባራዊነት የእነዚህ አደር ባይ ኢ-ኢትዮጵያዊ ባህሪ ተላባሽ ሊሂቃን ነን ባዮች የአንድ ቀን መፈንደቅያ ሊሆን ካልሆነ ዘላቂ ሰላምን ፍጹም አያመጣም። የዘላቂ ሰላም መንገድ አንድና አንድ ብቻ ነው። ይኸውም፣ ሁለቱ መንግሥታት አጎራባች መንደሮች በራሳቸው በነፃነት ተወያይተው ይህ የኛ ያኛው የናንተ ተባብለው ችካል እንዲያስቀምጡ የሚፈቅድ ስምምነት ለመፈራረም መደራደር ነው። የኤርትራ መንግሥት ይህንን ለመቀበል አሻፈረኝ ካለ ሰላም ፍለጋ ላይ እንደሌለና በአከባቢውም ሰላም ሊመጣ እንደማይችል በግልጽ አመላካች እንደሆነ በመረዳት ኢትዮጵያ ከሰላም ድርድሩ ምንም የምታገኘው ነገር እንደማይኖር ታውቆ ከአቶ ኢሳያስ መንግስት ድርድሩን ከማስቀምና ሌላ ምፍትሄ ከመፈለግ  ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሊላት መታወቅ አለበት።
2. በኤርትራ ታግተው የተወሰዱብን ከመቶ ኢሮቦችና 23 የዛላንበሳ አከባቢ ተወላጆች (ቁጥሩ ከዛ በላይ ሊሆንም ይቻላል) እስከ ዛሬ ድረስ ጠያቂ ባለቤት ሳያገኙ ቆይቷል። ዶ/ር ዓቢይ ሥልጣን እንደተረከቡ ካከናወኑዋቸው ታላላቅ ሥራዎች አንዱ ከየሄዱበት አገር ኢትዮጵያዊያን እስረኞችን ጭኖ መመለሳቸው ነው። ሳዑዲ ዓራቢያን፣ ከኒያን፣ ሱዳንና ግብጽን ይጠቅሷል። አሁንም፣ ከአቶ ኢሳያስ ጋር በቅርብ እንደሚገናኙ እየሰማን ነው። እዚህ ላይ አደራ የምንልዎት ከ20 ዓመታት በላይ ታግተው የጠፉብንን ኢትዮጵያዊያን ዜጎች አስፈትተው ይዘውልን እንዲመለሱ ከመጠየቅም በላይ በሕይወት የተማረኩት የኮለኔል በዛብህ ጴጥሮስ እና ሌሎች በተመሳሳይ መልክ የተወሰዱ ዜጎች ካሉ ሁኔታቸውንም እንዲያጣሩና ነጻ የሚወጡበት መንገድ እንዲፈልጉ  ነው።

<u>በመጨረሻ ለሰፊዉ የኢትዮጵያ ህዝብና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች የምናቀርበው ጥሪ፣</u> ለኢሮብ ህዝብና ለሌሎች በተመሳሳይ ሁናቴ ለሚገኙ የኢትዮጵያ ዜጎች ድጋፋቸውን እንዲቸሩ፣ እንዲሁም ለሉዓላውነታችንና ላንድነታችን አብሮ እንዲሰለፉ ነው።

እኛ ኢሮቦች እንደ አባቶቻችን ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ለኢትዮጵያዊነታችን መከፈል ያለበትን መስዋዕትነት ለመክፍል ዝግጁ ነን!!!

የኢትዮጵያ ዳርድንበርና ሉዓላዊነት እንደትናንቱ ዛሬም በልጆቿ ትብብር ተከብሮ ይኖራል!!!